**የጃኑዋሪ 31 እትም**

**በኤለመንተሪ ደረጃ የመድብለ-ቋንቋዎች ትምህርት ፕሮግራሞች/Language Immersion ከፌብሯሪ 1 ጀምሮ ማመልከቻዎች ተዘጋጅተዋል።**

**ለ2018–2019 የትምህርት ዓመት የማመልከቻ ጊዜ ገደብ ዓርብ፣ ሜይ 4 ነው። ወላጆችን ለማሳወቅ ከሜይ አጋማሽ ጀምሮ ደብዳቤዎች ይላካሉ።**

በ MCPS ለኤለመንተሪ ት/ቤት የመድብለ-ቋንቋዎች ትምህርት ፕሮግራሞች/language immersion ማመልከቻዎች አሁን ይገኛሉ። ለ2018–2019 የትምህርት አመት ለማመልከት የጊዜ ገደብ ዓርብ፣ ሜይ 4 ነው።

የኤሌሜንታሪ ት/ቤት የመድብለ-ቋንቋዎች ትምህርት ፕሮግራሞች/ language immersion የሚጀምሩት በሙዓለ ህፃናት ሆኖ የሚቀርቡትም በቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ እና በስፓኒሽ ነው። ዲስትሪክቱ ሶስት ስፓኒሽ፣ ሁለት ፈረንሳይኛ እና ሁለት ቻይንኛ የኤሌሜንታሪ መድብለ-ቋንቋ (ኢመርሽን) ፕሮግራሞች በካውንቲው ውስጥ በሰባት ቦታዎች ያቀርባል። ሁለቱ የፈረንሳይኛ ፕሮግራሞችና ከስፓኒሽ ፕሮግራሞች አንዱ ጠቅላላ መድብለ-ቋንቋ (ኢመርሽን) ናቸው። በጠቅላላ መድብለ-ቋንቋ (ኢመርሽን)፣ ሁሉም መሰረታዊ የትምህርት አይነቶች፣ የንባብ/የቋንቋ ኪነ ጥበባትን ጨምሮ፣ ትምህርት የሚቀርብባቸው በጥናት ቋንቋ ነው። ከስፓኒሽ ፕሮግራሞች ሁለቱና ሁለቱ የቻይንኛ ፕሮግራሞች ከፊል መድብለ-ቋንቋ (ኢመርሽን) ናቸው። በከፊል መድብለ-ቋንቋ (ኢመርሽን)፣ የተወሰኑ መሰረታዊ የትምህርት አይነቶች በትኩረቱ ቋንቋ ይቀርባሉ።

ስለ ኤሌሜንታሪ መድብለ-ቋንቋ (ኢመርሽን) ፕሮግራም ተጨማሪ መረጃ እና Immersion Interest Form (የመድብለ-ቋንቋ (ኢመርሽን) ማመልከቻ ቅጽ)ን ለማውረድ፣ Special Programs website ይጎብኙ። እንዲሁም ቅጾቹ አሁን በኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች ይገኛሉ። ስለፕሮግራሞቹ የበለጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማግኘትና ይበልጥ ለማወቅ ከፈለጉ እነዚህን የስብሰባ ዝርዝሮች ይመልከቱ፡-

http://www.montgomeryschoolsmd.org/uploadedFiles/curriculum/specialprograms/admissions/Immersion%20Interest%20Meeting%20for%20Web%20docx%20revised%201.18.18(1).pdf

በግንቦት ወር የማስታወቂያ ደብዳቤዎች ለወላጆች በፖስታ ይላካሉ። ከጊዜ ገደብ በኋላ የደረሱ ማመልከቻዎች እንደየአመጣጣቸው በመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ ይቀመጣሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ 301-592-2040 ይደውሉ።

[የኤሌሜንታሪ መድብለ-ቋንቋ (ኢመርሽን) ፕሮግራም]

**ሁለተኛው ዓመት "United We Learn" የተማሪዎች ውድድር በ MCPS ይካሄዳል።**

ተማሪዎች ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በቡድን ሆነው እንዲሰሩና ለእይታ የሚሆኑ የስነጥበባት ስራዎችን እና የስነጽሑፍ ውድድሮችን አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ እናደፋፍራለን። ውድድሩ ማርች 16 በ 5 p.m ይዘጋል።

MCPS ለእያንዳንዱ ተማሪ ስለወደፊታቸው ስኬታማነት የሚያስፈልጉ መጠቀሚያ/መገልገያዎችን (resources) የማግኘት እድል እንደሚኖራቸው ለማረጋገጥና ብዙሃነታችንን ለማክበር ቁርጠኞች ነን። ይህንኑ ቁርጠኝነታችንን ለማስፋፋት/ለማረጋገጥ የሁለተኛውን ዓመት "United We Learn: All Means All" የተሰኘውን ሥርአትአቀፍ የተማሪዎችን ውድድር MCPS ስፖንሰር ያደርጋል።

ስለ ሰው እኩልነት ጉዳይ እየዳሰሱ ብዙሃነትን ለማክበር ተማሪዎች የሚታዩ የስነጥበብ ሥራዎችን እና የቃላት ስነጽሑፎችን እንዲጠቀሙ ተጠይቀዋል። ውድድሩ ተማሪዎችን የሚያጋፍጠው ስለ እኩልነት/ሚዛናዊነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ጥልቀት ያለው ትንታኔ/ግምገማ እንዲያቀርቡና አመለካከቶች/ሁኔታዎች፣ ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ ባህሎች/ልማዶች፣ ሥርአት አቀፍ ድርጊቶች እና/ወይም ሁሉ ማለት ሁሉንም/ስለሁሉም ለሁሉም “All Means All.” የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ የህጋዊ ጉዳዮች አፈጻጸም ማጎልበት/ማዘግየት ወይም ይደግፍ እንደሆነ በጥልቀት እንዲያስቡ/እንዲተቹ ያደርጋል። ግባችን ተማሪዎች ስለ እኩልነት/ሚዛናዊነት በጥልቀት በመመራመር ፈጠራ፣ ገንቢና/መዋቅራዊ የተደራጀ አቀራረብ በመዘርጋት እኩልነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና የተወሰኑቱ እንደሌሎቹ በእኩልነት መጠቀሚያዎችን/መገልገያዎችን/resources የማግኘት እድል እንዳይኖራቸው ስለሚገድቡ መሰናክሎች በጥልቀት ለማሳየት ነው።

ውድድሩ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ለሚገኙ ተማሪዎች ክፍት ነው። የሚያቀርቧቸው መወዳደሪያዎች በየደረጃቸው (ኤሌሜንታሪ፣ መካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ) እና በሚዛናዊነት ይዳኛሉ። መወዳደሪያዎቹ በሁለት ተማሪዎችና ወይም ከዚያ በላይ በቡድን መቅረብ አለባቸው። የሚቀርቡት መወዳደሪያዎች በሚከተለው ዓይነት ረድፍ ተቀባይነት ይኖራቸዋል፦ በቃላት ስነጽሑፍ እና በሚታይ ሥዕላዊ ስነጥበብ። ተጨማሪ ዝርዝሮች በውድድሩ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛሉ።

**ውድድሩ የተከፈተው ሰኞ ጃኑዋሪ 29 ሲሆን ማርች 16 ዓርብ 5 p.m ላይ ይዘጋል።**

**ለልዩ ትምህርት ስለተደረገ አስተዋፅኦ እውቅና መስጠት**

**ለልዩ ትምህርት ሽልማቶች ጥቆማ ለማቅረብ እርግጠኛ ይሁኑ። የሥራ ባልደረቦች፣ ተማሪዎች እና ወላጆች ልዩ እርዳታና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ አስተዋጽኦ ያደረጉ ግለሰቦችን እና ፕሮግራሞችን አክብሮት ለመስጠት ይችላሉ። ቀነ ገደቡ ዓርብ ማርች 23 ነው።**

**የሥራ ባልደረቦች፣ ተማሪዎች እና ወላጆች ልዩ እርዳታና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተቀባይነት እንዲያገኙ እና ስኬታማ እንዲሆኑ አስተዋጽኦ ያደረጉ ግለሰቦችን እውቅና ለመስጠት ጥቆማ እንዲያቀርቡ እናደፋፍራለን።**

እውቅናዎቹ የሚሰጡት በ Montgomery County Council of PTAs (የ PTA ምክር ቤት) (MCCPTA) ልዩ የትምህርት ኮሚቴ ነው። ሜይ 14 በሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚካሄደው እውቅና የመስጠት ሥነ-ሥርዓት ስንክልና ባለባቸው ተማሪዎች ላይ ኢንቨስት በማድረግ ያሉትን ጠቀሜታዎች በመዘርዘር እውቅና ይሰጣል።

ጥቆማዎች መቅረብ ያለባቸው በአራት ፈርጆች ነው፡- የት/ቤት ሰራተኞች፣ ፕሮግራሞች፣ ወላጆች እና ተማሪዎች። ጥቆማዎቹ በኤሌክትሮኒክስ እንዲቀርቡ ይበልጥ ይመረጣል።

**የማመልከቻዎች የጊዜ ገደብ አርብ፣ ማርች 23 ነው።** የእጩዎች ጥቆማ በሥራ ባልደረቦች፣ በወላጆች ወይም በተማሪዎች ሊቀርብ ይችላል። በኢ-ሜይል ተያይዞ በሚከተለው አድራሻ ለ Jeanne Taylor ማቅረብ/መላክ ያስፈልጋል፦ Jeanne Taylor, or by hard copy to the Montgomery County Council of PTAs, P.O. Box 10754, Rockville, MD 20849.

በኤሌክትሮኒክ ጥቆማ ለማቅረብ ካልቻሉ፣ የተሞላውን የጥቆማ ቅጽ እና የመጠቆሚያ መግለጫ ከመደገፊያ ጽሑፍ ጋር ለ፦ MCCPTA office: Montgomery County Council of PTAs, P.O. Box 10754, Rockville, MD 20849 ለመላክ ይችላሉ።

የበለጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማግኘት Jeanne Taylor ን ያግኙ፦

MCCPTA Special Education Awards Nomination Form 2017-2018/ለልዩ ትምህርት ሽልማት ጥቆማ ማቅረቢያ ቅጽ

**መከባበርን ስለ መምረጥ ጤናማ የለጋ ወጣቶች የፍቅር ግንኙነት ፍሬ ጉዳዮችን አጉልቶ ያሳያል።**

የኤፕሪል 15 ዝግጅት በለጋ ወጣቶች ዙርያ ስለ ፍቅር ግንኙነት ጠብና ረብሻ የችግሮችን መንስኤዎች በመመርመር የሚያተኩር ይሆናል። ለተማሪዎች፣ ወላጆች፣ አስተማሪዎች እና ለወጣት አገልግሎት ሰጪዎች መጠቀሚያ/resource fair እና አውደጥናቶችን ያካትታል።

እሑድ ኤፕሪል 15 በሪቻርድ ሞንጎመሪ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Richard Montgomery High School) የሚካሄደው 9ኛው “መከባበርን መምረጥ ሞንትጎመሪ” ዓመታዊ ኮንፈረንስ የሚካሄድበት ጊዜ

ተቃርቧል። ዝግጅቱ ትኩረት የሚያደርግባቸው በለጋ ወጣቶች ዙርያ የፍቅር ውሎ ረብሻና ጠብ ችግሮችንና የመንስኤ ምክንያቶችን ለመመርመርና መገልገያዎች/resource fair ላይ ነው። ከእኩለ ቀን በኋላ-1 p.m ላይ ይጀመራል። ኮንፈረንሱ ለተማሪዎች፣ለወላጆች፣ ለአስተማሪዎች እና ለወጣት አገልግሎት ሰጪዎች ከ 1–4:30 p.m የሚካሄዱ የውይይት አውደጥናቶችንም ያካትታል። ኮንፈረንሱን ለመካፈል ምዝገባ የሚከፈተው ሐሙስ ማርች 1 ነው።
https://docs.google.com/forms/d/e/1FAIpQLSfn-rNQEt06tgfXpiahEDyxRXQqrFbFQUF53KcN0RgXOznkVA/viewform

መከባበርን መምረጥ የቪድኦ ውድድር/Choose Respect video PSA አሁን ተወዳዳሪዎችን እየተቀበለ ነው፤ አሸናፊዎች ለአንድ ደቂቃ ቪዲዮ እስከ $1,000 ገንዘብ ያገኛሉ። በዚህ ውድድር ወጣት ልጆች ስለ ህዝባዊ አገልግሎት ኦርጅናል ቪዲዮ ማስታወቂያ አዘጋጅተው ስለ ፍቅረኛ ወጣት ልጆች ጥቃት እና ስለ ወጣት ልጆች የቤት ውስጥ ጭቅጭቅና ጠብ ትምህርት ሰጪ/ግንዛቤ ለመስጠት የሚያስችል የፈጠራ ችሎታቸውን ተጠቅመው የሚጋፈጡት ነው። ከስድስተኛ እስከ 12ኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች ክፍት ነው፣ ተማሪዎች ለብቻቸው/በየግላቸውም ይሁን ወይም በቡድን በውድድሩ ለመሳተፍ ይችላሉ። **የሚያቀርቡበት ቀነ-ገደብ ዓርብ ማርች 16/2018 ነው።** ተጨማሪ መረጃዎች እዚህ ይገኛሉ።

**የሰመር ካምፕ ምዝገባ ተጀምሯል።**

በካውንቲው ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ይኖራሉ። ምዝገባ አሁን ክፍት ነው።

የሞንጎመሪ ካውንቲ መዝናኛ እና የሞንጎመሪ ፓርኮች በዚህ ሰመር ወቅት ለወጣቶች ጤናማ የአኗኗር ዘይቤዎችን ለማስተዋወቅ በመቶዎች የሚቆጠሩ ካምፖች አሏቸዉ ። የካውንቲ ሰፈሮች በካውንቲው ከዳር እስከዳር ለሚገኙ ቤተሰቦች ርካሽ፣ አስደሳች እና አመቺ ናቸው። እንቅስቃሴዎች ለተለያዩ ፍላጎቶች፣ የችሎታ ደረጃዎችና እድሜዎች ተጢነው የሚቀርቡ ናቸው። የሰመር ፕሮግራሞች የሚያካትቱት የውኃ ውስጥ እንቅስቃሴዎችን/aquatics የስነጥበብ ሥራዎችን፣ ተፈጥሮ፣ ማሰስና መመራመር፣ ምግብ ማዘጋጀት/ማብሰል እና ስፖርት ናቸው።

የሞንጎመሪ ካውንቲ ካምፕ መምሪያ ለማየት እዚህ ጠቅ/ክሊክ ያድርጉ። ምዝገባ አሁን እየተካሄደ ስለሆነ ActiveMontgomery.org ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።

የመመሪያው የታተሙ ቅጂዎች በማህበረሰብ መዝናኛ ማእከሎች፣ የመናፈሻ ቦታ መገልገያዎች፣ የውሃ መዋኛ ቦታዎች፣ በካውንቲ ማእከሎችና የህዝብ ቤተ መፃህፍት በተጨማሪ ይገኛሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ 240-777-6840 ይደውሉ።

የ2018 የደህንነት ጥበቃ ጓድ ሰፈር/የ2018 የደህንነት ፓትሮል ካምፕ

የMontgomery County Police School Safety Unit/የሞንጎመሪ ካዉንቲ ፖሊስ የት/ቤት ደህንነት ክፍል ለሳምንት የሚቆይ የደህንነት ፓትሮል ካምፕ በጁን እና በጁላይ ያዘጋጃል። ይህ ካምፕ ውጤታማ

የደህንነት ጥበቃ ጓድ ለመሆን የተለያዩ ሃላፊነቶችን ለመማር ፍላጎት ላላቸው የ5ኛ ክፍል አዲስ ገቢ የጥበቃ ጓዶች ነው። ይህ ለአንድ ሣምንት የሚዘልቅ ካምፕ የሚካሄደው በ Summit Lake Camp in Emmittsburg, Md ሲሆን ዋጋው ለአንድ ጊዜ $325 per session ነው። ወደ ካምፑ የደርሶ-መልስ ትራንስፖርት ይቀርባል። ሁለት ክፍለ ጊዜያት ይኖራሉ፦ ከጁን 25-29 እና ከ ጁላይ 16-20፣ ወላጆች ከእነዚህ ለአንድኛው ክፍለጊዜ ብቻ ለመመዝገብ ትችላላችሁ። ምዝገባ መጀመርያ የደረሰ፣ የመጀመሪያውን አገልግሎት ያገኛል በሚለው መርህ መሰረት ነው።

[የ2018 የደህንነት ጥበቃ ጓድ ሰፈር/ፓትሮል ካምፕ]